# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

## የባንኩ አጭር የብድር መመሪያ

# 1. መግቢያ

የልማት ባንክ አገልግሎት በኢትዮጵያ ከተጀመረ አንድ ምዕተ-ዓመት ያህል ሆኖታል፡፡ በሀገሪቱ የመጀመሪያው የሆነው የእርሻና ንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ማኀበር ተቋቁሞ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ከግንቦት 23 ቀን 1901 ዓ/ም /እ.ኤ.አ. ግንቦት 31 ቀን 1909/ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የሀገራችንን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ልማት በማገዝ በየወቅቱ የተቋቋሙትና የተዋሃዱት የልማት ባንኮች ከፍተኛ የልማት ተግባር ማከናወናቸው የሚታወቅ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል አንዱ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ነው፡፡

ይህ በረዥም ጊዜ የብድር አገልግሎት ዘመኑ ከፍተኛ ልምድ ያካበተው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአጭር፤ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የልማት ብድሮችን በመስጠት በሀገሪቱ ውስጥ ከተሰማሩ የመንግስት የፋይናንስ ተቋማት መካከል አንዱ ነው፡፡ ባንኩን ከሌሎች የፋይናንስ ተቋሞች ልዩ የሚያደርገው ባሕርይ በፕሮጀክት ላይ የተመሠረተ ብድር የመስጠት ልምዱ ነው፡፡ በባንኩ ብድር የሚቋቋሙ ፕሮጀክቶች በጥንቃቄ የሚመረጡ፤ የሚዘጋጁ፤ በሚገባ የሚጠኑ፤ የቅርብ ክትትል የሚደረግባቸውና እንዲሁም በተለያዩ የመለኪያ መስፈርቶች የሚመዘኑና የሚገመገሙ ናቸው፡፡

የባንኩ ድርጅታዊ አቋም በመንግስት የልማት ድርጅት አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ፤ የሥራ አመራር ቦርድ፤ ፕሬዝዳንትና የባንኩን ሠራተኞች የያዘ ነው፡፡ ልማት ባንኩ በመላው ሀገሪቱ ውስጥ ስትራቴጂካዊ በሆኑ ቦታዎች የተቋቋሙ የሪጅንና የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች አሉት፡፡ ባንኩ ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋ ለማድረግ በቅርቡ ለሁሉም ሪጅኖቹ ና ቅርንጫፎቹ እስከተወሰነ ደረጃ ፕሮጀክቶችን የማጥናት፤ ዋስትና የመያዝና ብድር የመስጠት ሥልጣናቸውን ከፍ አድርጎላቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ባለው የረጅም ዓመታት አገልግሎቱ የኢንቨስትመንት ብድርን በመስጠት የዳበረ ልምድ ያለው ባንክ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ግዴታውም ከውጭ ምንጮች በግልም ሆነ በጋራ ለሀገር ውስጥ የልማት ፕሮግራም የሚመደበውን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ በማድረስ የብድር መተላለፊያ ዋነኛ ተቋም ለመሆን በቅቷል፡፡

ባንኩ በአሁኑ ጊዜ የመንግስትን የትኩረት አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ለእርሻ፣ ለአግሮ ኢንዱስትሪና ለመፈብረኪያ (Manufacturing) ኢንዱስትሪዎች በተለይም ለውጭ ምንዛሪ ግኝት ለሚረዱ ፕሮጀክቶች የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት ብድር አገልግሎት የመስጠቱን ሥራ ዋና ተግባሩ አድርጎ በመንቀሳቀስ ላይ ነው፡፡

## 2. <u>ራዕይ</u>

ሀገራዊውን የልማት አጀንዳ በማሳካት ረገድ ዓለም-አቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ የፕሮጀክት ፋይናንስ ማዕከል መሆን፡፡

## 3. <u>ተልዕኮ</u>

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሀገሪቱን የልማት አጀንዳ እውን ለማድረግ የተቋቋመ ልዩ ባንክ ነው፡፡ ስለሆነም መንግስት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የልማት ዘርፎች እና በደምበኞች ፍላጎት ላይ ተመስርተው ለሚቋቋሙ ፕሮጀክቶች ልዩ ትኩረት በማድረግ የብድር አገልግሎት ይሰጣል፡፡

ባንኩ ድርጅታዊ ሕልውናውን እያረጋገጠ የሰው ኃይል አቅሙን እና የሙያ ብቃቱን እየገነባ የልማት ብድር አገልግሎቱን የበለጠ በማስፋፋት የደንበኞቹን ፍላጎት ያረካል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እንደማንኛውም ዘመናዊ ድርጅት በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እየታገዘ ለማኀበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት እድገት እንደሚጥር ሁሉ እንዲሁም ለተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ እና ደህንነት የሚቆረቆር ልዩ የገንዘብ ተቋም ነው፡፡

## 4. <u>እሴቶች</u>

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እሴቶች በሠራተኛውና በአመራሩ በጋራ የተያዙና መተግበር ያለባቸው እምነቶች ናቸው፡፡ እሴቶቹ የግለሰብና የሙያ ድምር ውጤቶችና በሁሉም ዘንድ የሠረፁ ናቸው፡፡ ስለሆነም በባንኩ ሠራተኞች የሚገለፁት እሴቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ደምበኛ ተኮር ነን
- ልቆ መገኘት ለየት የሚያደርገን ባህሪ ነው

- ሀቀኝነት ተመን የሌለው ሀብታችን ነው
- የቡድን ሥራ እና አዳዲስ ግኝቶችን መጠቀም የውጤታማነታችን ምሰሶዎች ናቸው
- አካባቢን መጠበቅ አንዱ የባንካችን የብድር መስፈርት ነው
- ባንኩ ለሠራተኞቹ ከፍ ያለ ዋጋ ይሰጣል
- ለድርጅታችን ተልዕኮ መሳካት ያለን ቁርጠኝነት መለያችን ነው
- ለባንኩ መለወጥ የአመለካከት ለውጥ፤ ሥነ ምግባርና የተሻለ የሥራ ባህል ወሳኝ ኃይሎች ናቸው

## 5. <u>የባንኩ ዓላማዎች (Objectives)</u>

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች፤

- የኢንቨስትመንት እና የአጭር ጊዜ ብድርን በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላላቸውና ውጤታማ ለሆኑ ፕሮጀክቶች መስጠት
- ከአገር ውስጥና ከውጭ ምንጭ ለልማት የሚውል ገንዘብ ማሰባሰብ
- የአደራ ገንዘብ ማስተዳደር
- የአክሲዮን ድርሻ በመያዝ በኢንቨስትመንት መሳተፍ
- ለተበዳሪዎቹ የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር የባንክ አገልግሎት መስጠት
- የጊዜ ገደብ ያለው ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል
- ለብድሮችና ለሌሎች መሰል የገንዘብ ግዴታዎች ዋስ መሆን
- በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ተከፋይ የሚሆኑ የሐዋላ ወረቀቶች፤ የገንዘብ ሰነዶችና የተስፋ ሰነዶች ማውጣት፣ መቀበል፣ በቅናሽ መውሰድ መግዛትና መሸጥ
- ቦንድ ማውጣትና መሸጥ
- እንደ ባለአደራ ወይም እንደ ንብረት ተቀባይና ጠባቂ መስራት
- የቴክኒክና የሥራ አመራር ምክር አገልግሎት መስጠት
- በአገር ውስጥና በውጭ ባንኮች ሂሣብ መክፈትና ማንቀሳቀስ
- ሌሎች የተለመዱ የልማት ባንክ ሥራዎችን ማከናወን

## 6. የባንኩ ካፒታል

ለባንኩ የተፈቀደው ካፒታል ብር 3,000,000,000 /ሶስት ቢሊዮን ብር/ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ ብር 1.8 ቢሊዮን /አንድ ነጥብ ስምንት  ቢሊዮን ብር/ የተከፈለ ካፒታል ነው::

## 7. ባንኩ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች

### 7.1 የብድር አገልግሎት

- ባንኩ የብድር ጠያቂዎችን ፕሮጀክቶች ትርፋማነት ለማረጋገጥ አስተማማኝ በሆነ ዘዴ አስቀድሞ ጥናት ያካሂዳል::
- ለአዳዲስ አመልካቾችና ለነባር ደንበኞች የምክርና የቴክኒክ አገልግሎትም ይሰጣል::

### 7.2 የባንክ አገልግሎት

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች አንዱ የባንክ አገልግሎት ነው፤ የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ገንዘብም ይቀበላል፤ የተንቀሳቃሽና የቁጠባ ሂሣብ፤ የሐዋላና ኤልሲ (L/C) አገልግሎቶችን ይሰጣል::

የባንኩ ደንበኞች ከውጭ ሀገር የማምረቻ መሣሪያዎችንና ጥሬ ዕቃዎችን ወደ ሀገር  ውስጥ ማስገባት እንዲችሉና ምርቶቻቸውንም ወደውጭ እንዲልኩ የኤልሲ (L/C) እና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን በመስጠት አስፈላጊውን ዕገዛ ያደርጋል::

## 8. ባንኩ ብድር የሚሰጣቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በዘመናዊ ደረጃ ለሚቋቋሙ ለእርሻ፣ ለማቀነባበሪያ /Agro Processing/& ለመፈብረኪያ እና የከበሩ ማዕድናት ልማት /Manufacturing and Extractive Industries/ ኢንዱስትሪዎች በተለይም ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ብድር ይሰጣል::

የሚከተሉት ንዑስ የኢኮኖሚ ዘርፎች በባንኩ የብድር አገልግሎት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው::

## ዘመናዊ እርሻ ልማቶች:-

- የአትክልት ልማቶች (አትክልቶች፥ ፍራፍሬዎች፣ እንጉዳይ (mushroom) እና የመሳሰሉት፤
- የምርጥ ዘር ማራባት ልማት፤
- የምግብ እህል እርሻ ልማት (የስንዴ፣ የበቆሎ፣ የሩዝና የመሳሰሉት)፤
- የቡና ተክልና ልማት፤
- የመስኖ ጥጥ እርሻ ልማት፤
- የዕፅዋት ነዳጅ አትክልት ልማት (Bio fuel plantation)፤
- የሻይ ተክልና ልማት፤
- የዶሮ ርባታና ማቀነባበሪያ /Processing/፤
- የፓልም ዘይት ተክልና ማቀነባበሪያ፤
- የጎማ ዛፍ ተክልና ልማት፤
- የሐር ልማት (silk warm farming)፤
- የአዞ ርባታና ማቀነባበሪያ፤
- የከብት ርባታና ልማት፤
- የቅባት እህሎች እርሻና ማቀነባበሪያ /ሰሊጥን ጨምሮ/፤
- የሸንኮራ አገዳና ተመሳሳይ ተክል ልማትና ማቀነባበሪያ
- የንብ ርባታ፤
- የቅመማቅመሞች፣ የመድሐኒት ተክሎችና ልዩ (essential) የዘይት ምርቶች መጭመቂያና ማቀነባበሪያ፤
- የቃጫ ተክል ልማትና ማቀነባበሪያ፤
- ለወረቀትና ለወረቀት ውጤቶች ምርትና ለግንባታ የሚሆን ቀርቀሀ ተክል ልማት፤
- የአሳ ርባታና ማቀነባበሪያ፤
- የአሳማ ርባታና ማቀነባበሪያ፤
- የሰጎንና ዳክዬ ርባታና ማቀነባበሪያ፤

## የእርሻ ውጤቶችን ማቀነባበሪያ (Agro Processing)

- የምግብ ማቀነባበሪያዎች፤ የፓስታ ምርቶችንና ተያያዥነት ያላቸው፣ የዱቄት ፋብሪካዎችን የያዙ፤
- የጥጥ ምርትና መዳመጫ ኘሮጀክት፤
- የወተት ተዋፅኦዎች ምርት፤ የተቀነባበረ ወተት፤ አይብና ቅቤ ለሚያመርቱ፤
- የእንስሳት መኖ ምርትና ማቀነባበሪያ
- የሥጋ ምርት ከብት ልማትና ማቀነባበሪያ እንዲሁም አሽጎ መሸጥ (Canning)
- የዶሮ ሀብት ልማት፡- የዶሮ እርድ ስጋ፣ ዕንቁላልና የአንድ ቀን ጫጩት ምርት፤
- የቡና ማቀነባበሪያ፤ መቁላትና መፍጨት
- የምግብ ዘይት መጭመቂያና ማቀነባበሪያ ማርጋሪን፣ የተጣራ የምግብ ዘይት፣ ሰሊጥ (ጣሂና) (Tehina)፤
- የፍራፍሬ ጭማቂ ምርት፤
- የተፈጥሮ ዘይት (bio fuel) ምርትና ማቀነባበሪያ፤
- የብቅል ምርት ማቀነባበሪያ፤
- የተፈጥሮ ማዳበሪያ ምርት፤

## የመፈብረኪያና የማጣሪያ ኢንዱስትሪዎች (Manufacturing and Extractive Industries)

- የመጠጥ፣ የማዕድንና የጠርሙስ ውሃ ምርት ፋብሪካዎች፤
- የጨርቃጨርቅ እና ጣቃ ፋብሪካዎች (Textiles & fabrics)፤
- የአልባሳት ፋብሪካዎች (garment factories)፤
- ያለቀላቸው ቆዳዎችና የቆዳ ወጤቶች ፋብሪካዎች (Leather and Leather factories)፤
- የወረቀትና የወረቀት ውጤቶች ፋብሪካዎች፤
- የጎማና የጎማ ውጤቶች ፋብሪካ ፤
- ብረት ያልሆኑና ሌሎች የግንባታ ዕቃዎች ማምረቻ ፋብሪካ ፡- ሲሚንቶ፣ ጅብሰም፣ እምነበረድ፣ ሸክላ፣ መስታወት የመሳሰሉትን የሚያመርቱ፣
- የብረታ ብረት መፈብረኪያና ማቀነባበሪያ ፋብሪካ

- የከበሩ ብረት ማዕድናት ማውጫ ፋብሪካ :- ጀምስቶንስ፣ ታንታለም፣ ወርቅና የመሳሰሉት (gemstones, tantalum, gold, etc)
- የተቀነባበሩ የብረት ውጤቶች ፋብሪካ (Fabricated metal products factory)
- የተሽከርካሪዎችና የተሳቢዎች መገጣጠሚያ ፋብሪካ
- የማሽኒያ ዕቃዎች ማምረቻ ፋብሪካ
- ከእንፋሎት (geothermal)፣ ከንፋስና ከፀሐይ ኤሌክትሪክ ለሚያመርቱ ፋብሪካዎች፤
- የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን የሚያመርት ፋብሪካ ፤
- የጽዳት ዕቃዎች (sanitary material) ፋብሪካ
- ለኤሌክትሪክ ማመንጫ የሚውሉ አነስተኛ ግድቦች፤

## 9. ባንኩ የሚሰጣቸው የብድር ዓይነቶች

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የፋይናንስና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነታቸው በጥናት ለተረጋገጠላቸው፤ በአካባቢ ተስማሚነታቸው፣ በሥራ ዕድል ፈጣሪነታቸውና በሌሎችም ማህበራዊ ጠቀሜታቸው ለተመረጡ፣ ኘሮጀክቶች የረጅምና የመካከለኛ እንዲሁም የአጭር ጊዜ የሥራ ማስኬጃ ብድሮችን ይሰጣል:: የብድሩ ጊዜ (term of loan) ግን እንደየኘሮጀክቱ ልዩ ፍላጎትና አስፈላጊነት እየታየ የሚወሰን ነው:: ባንኩ የሚሰጠው ብድር በጊዜ ተከፍሎ ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል::

### 9.1 የረጅም ጊዜ ብድር:

እስከ ሃያ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የእፎይታ ጊዜን ጨምሮ ተከፍሎ የሚያልቅ ነው:: ቋሚ የሥራ ማስኬጃ እንደ ኢንቨስትመንት ከፒታል የሚቆጠር ሲሆን ከ 5 - 15 ዓመታት ባለው የክፍያ ጌዜ ተመላሽ የሚደረግ ነው:: የረጅም ጊዜ ብድር ዓላማውም ለፋብሪካዎች ግንባታና ለማምረቻ መሣሪያ መግዣ፤ ለመስኖ እርሻ ልማት፤ ለቋሚ ሰብሎች ልማትና ለእርሻ መሣሪያዎች መግዣ፤ ለትራንስፖርትና መገናኛ እንዲሁም ከፕሮጀክቱ ጋር ለተያያዙ መሠረተ ልማቶች ማቋቋሚያ ወይም መግዢያ የሚውል ነው::

## 9.2 የመካከለኛ ጊዜ ብድር፤

ሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ ሲሆን ዓላማውም፤ ለሕንፃ ግንባታ፤ ለማምረቻ መሣሪያ፤ ለቢሮ መሣሪያዎች፤ ለቢሮ መገልገያዎች እንዲሁም ለተሽከርካሪዎች መግዣና ለመሳሰሉት የሚውል ነው።

## 9.3 የሥራ ማስኬጃ ብድር፤

በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚከፈል የብድር ዓይነት ሲሆን ዓላማውም ለሥራ ማስኬጃ የሚውል ነው። የሥራ ማስኬጃ ብድር ለነባር ደንበኞች ብቻ የሚሰጥ ሲሆን ከግብዓት ግ ¡ እስከ ሽያጭ ባለው መ‹ከል የሚፈጠር የገንዘብ እጥረትን ለማቃለል@ በማምረት አቅም መጨመር ጋር ተያይዞ ለሚያስፈልግ ተጨማሪ ግብዓት ማሟያና ለአጭር ጊዜ የገንዘብ ችግር መሸፈኛ የሚሰጥ ነው።

REVISED
10:09 am, Sep 03, 2010

# 10. ለመበደር የሚያበቁ ሁኔታዎችና የግል መዋጮዎች

10.1 ከባንኩ ብድር ለማግኘት የሚሹ አዳዲስ ተበዳሪዎች ከፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጭ ውስጥ ቢያንስ 30% የሚሆነውን ማዋጣት ይጠበቅባቸዋል።

10.2 ቅድሚያ ትኩረት ለሚሰጣቸው አዳዲስ ፕሮጀክቶች ማቋቋሚያ ብድር የሚሹ ተበዳሪዎች ከአጠቃላይ የፕሮጀክት ወጭ ውስጥ ቢያንስ 30% የሚሆነውን በጥሬ ገንዘብ ማዋጣት ይጠበቅባቸዋል። የጥሬ ገንዘብ መዋጮውን በቅድሚያ አንድ ጊዜ ወይም በመከፋፈል የብድር ውሉ ከተፈረመ ጀምሮ ከ6 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ደንበኛው በቅድሚያ ማዋጣት አለበት። የባንኩ መዋጮ ቢበዛ የፕሮጀክቱን አጠቃላይ ወጭ 70% የሚሸፍን ሲሆን ብድሩ የሚለቀቀው ከደንበኛው የሚፈለገው 30% መዋጮ ተዋጥቶ ሥራ ላይ መዋሉ ከተረጋገጠ በኋላ ነው። ሆኖም ስትራቴጃዊ የሆኑ ፕሮጀክቶች ከሆኑና የግንባታ ሂደታቸው ደረጃ በደረጃ በረጅም ጊዜ የሚተገበር ሲሆንና በአንድ ጊዜ ማዋጣት ከተቸገሩ ጉዳያቸው ለቦርድ ቀርቦ የሚታይበት አግባብ ሊኖር ይችላል።

10.3 በማምረት ተግባር ላይ ያሉ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ለማስፋፋት የሚሹ ተበዳሪዎች ሆነው ፕሮጀክታቸው በሌላ ብድር ዋስትና ያልተያዘና አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ሀብት ግምት የፕሮጀክቱን ወጭ 40% የሚሸፍን ከሆነ የማስፋፊያውን ወጭ 100% ባንኩ ፋይናንስ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ይህም ማለት የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጭ መዋጮ ነባሩንም ጨምሮ 60:40 ይሆናል፡፡ ደንበኛው በሚያስፋፋው ፕሮጀክት ላይ የሚፈጠር የገንዘብ ክፍተትን ለመሙላት ለሚያዋጣው ተጨማሪ የጥሬ ገንዘብ መዋጮ ከባንኩ በ70:30 የድርሻ ሚዛን መሠረት ተጨማሪ ብድር ሊያገኝ ይችላል፡፡

10.4 ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ለማቋቋም የሚሹና ከፕሮጀክቱ ውጭ በሌላ ዋስትና ያልተያዘና ገቢ የሚያስገኝ /ለምሳሌ የኪራይ ገቢ ያለው/ ድርጅት ያላቸው ተበዳሪዎች የድርጅታቸው ሀብት ግምት የፕሮጀክቱን አጠቃላይ ወጭ 40% የሚሸፍን ከሆነ የሚቋቋመውን ፕሮጀክት ወጭ 100% ባንኩ ፋይናንስ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ብድሩ ከድርጅቱና ከፕሮጀክቱ በሚገኝ ገቢ ተከፋይ ይሆናል፡፡

10.5 ለተቋቋሙ ኘሮጀክቶች ክፍያ ወይም የሚሸጥ ኘሮጀክትን ለመግዛት የሚቀርብን ጥያቄ ባንኩ አያስተናግድም፡፡

## 11. ብድርን ስለመግዛት

11.1 የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በሌሎች የሀገር ውስጥ ባንኮች የተሰጠ ብድርን ሊገዛ ይችላል፡፡ ሆኖም ባንኩ የሚገዛው ኘሮጀክት፤

- ውጤታማ/ በሥራ ላይ ያለ መሆን አለበት፡፡
- በባንኩ ቅድሚያ የሚሰጠው ክፍለ ኢኮኖሚ (priority sector) ኘሮጀክት መሆን አለበት፡፡

11.2 የሌላ ባንክ ተበዳሪዎች ብድራቸውን ወደ ኢትዮጵያ ልማት ባንክ ማዛወር የሚችሉት በነበሩበት ባንክ ውስጥ ጥሩ የብድር አከፋፈል ዲስኘሊን ኖሯቸው በሚያጨናንቅ የብድር አከፋፈልና ሌሎች ግዴታዎች የተነሳ የኘሮጀክቱን ህልውና የሚፈታተን ሁኔታ መኖሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡

11.3 ባንኩ የአጭር ጊዜ ብድሮችን ማለትም የንግድ ሥራ ብድሮችን (Merchandise Loans) ሌተር ኦፍ ክሬዲት (Letter of Credit)፣ ኦቨር ድራፍት ብድሮችን (Over draft loans) የቅድሚያና ድህረ የመርከብ ጭነት ክፍያን አይገዛም፤

11.4 የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በውጭ ባንኮች የተሰጡ ብድሮችን አይገዛም፤

11.5 የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሁለተኛ ደረጃ ዋስትናን አይቀበልም፡፡

## 12. አዲስ ኘሮጀክት ከሚያቋቁሙ አመልካቾች የሚፈለጉ መረጃዎች

ማንኛውም ብድር ጠያቂ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መግለጫዎች በአግባቡ ተገንዝቦ ጥያቄ ሲያቀርብ የሚፈለጉት መረጃዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ምክንያቱም የተፈላጊ መረጃዎችና ዶክመንቶች ተሟልተው መቅረብ ባንኩ ለደንበኛው ቀልጣፋና ብቁ አገልግሎት መስጠት ያስችለዋል፡፡

### 12.1. የሥራ ፈቃድ

12.1.1 እንደኘሮጀክቱ ዓይነት አግባብ ካለው የመንግሥት አካል ጊዜያዊ/ቋሚ/ የሥራ ፈቃድ

12.1.2 ዋና የምዝገባ ምስክር ወረቀት

12.1.3 ከሚመለከተው የፌደራል /የክልል/ የመንግሥት ባለሥልጣን የኢንቨስትመንት የምስክር ወረቀት

12.1.4 ታክስ ለመክፈል የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት (TIN)

12.1.5 የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርቲፊኬት (VAT)

12.1.6 ታክስ የከፈለ መሆኑን ማረጋገጫ ደብዳቤ /በሥራ ላይ ላለ ፕሮጀክት/

12.1.7 ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ኘሮጀክቱ በሚቋቋምበት አካባቢ ሊያደርስ የሚችለውን ተጽእኖ አስመልክቶ የተሰጠ የጽሑፍ ማስረጃ

## 12.2 መሬት

12.2.1 የመሬት ይዞታው በኪራይ ውል የተገኘ ከሆነ፤ አግባብ ካለው የመንግሥት አካል ጋር የተደረገ የኪራይ ውል ስምምነት ማረጋገጫ

12.2.2 ኘሮጀክቱ የሚቋቋመው በከተማ ክልል ውስጥ ከሆነ የከተማ ቦታ የይዞታ ምስክር ወረቀት/ካርታ/ እና አግባብ ባለው ባለሥልጣን የፀደቀ የግንባታ ፈቃድ፤

12.2.3 በገጠር ለሚቋቋመው ኘሮጀክት የመሬት ኪራይ ውል ከአርሶ አደሮቹ ጋር ስምምነት ከማድረግ ባሻገር በሚመለከተው የመንግሥት አካል መጽደቅ አለበት፡፡

12.2.4 የኘሮጀክቱ አቀማመጥ (Site Plan of the Project) /ለእርሻ ብድሮች ብቻ/

## 12.3. መተማመኛ /Margin of Safety/

ለምርቱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቋሚ ንብረቶች በሊዝ የሚገኙ ከሆነ ባንኩ የ5 ዓመት የተሰጠ መተማመኛ ይጠይቃል፡፡ መተማመኛውም ከሚመለከተው የመንግሥት ባለሥልጣን ሆኖ የባንኩ ብድር ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሚቆይና ባንኩ የሊዝ መብቱን ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የሚፈቅድ መሆን አለበት፡፡

## 12.4 ምህንድስና

12.4.1 የኮንስትራክሽን ኘላን (Blue Print) የሚያስፈልግ ሲሆን ፕላኑ መሠራት ያለበት ፈቃድ ባለው አማካሪ ድርጅት ነው፡፡ ይህም በከፍተኛ አማካሪ ድርጅት መጽደቅ አለበት፡፡ /ደረጃ 3 አማካሪ የሠራው ደረጃ 2 ባለው አማካሪ መጽደቅ አለበት፡፡ ደረጃ 2 አማካሪ የሠራው በደረጃ 1 አማካሪ መጽደቅ አለበት፡፡ ደረጃ 1 አማካሪ የሠራው ግን ከፍተኛ አጽዳቂ አያስፈልገውም/፡፡ የግንባታው ፕላን ማህተም የተመታና በሚመለከተው የመንግስት አካል የተፈረመበት መሆን አለበት፡፡

12.4.2 የግንባታ ሥራ መሠራት ያለበት ፈቃድ ባለው ኮንትራክተር ሲሆን፣ የተደረገ ስምምነትና የአከፋፈል ሁኔታ መቅረብ አለበት፡፡

12.4.3 የግንባታ ኘላን ሊይዛቸው የሚገቡ ዶክመንቶች

12.4.3.1 አርክቴክቸራል ኘላን

12.4.3.2 እስትራክቸራል ኘላን

12.4.3.3 የኤሌክትሪክ ኘላን

12.4.3.4 የፍሳሽ /ሳኒተሪ/ ሜካኒካል/ኘላን

12.4.3.5 የእርሻ ኘሮጀክት የውስጥ መንገድ ኘላን

12.4.3.6 ኘሮጀክቱ በመስኖ የሚለማ ከሆነ የውሃ መውረጃ /ቦይ/ ኘላን

12.4.3.7 የመሬት ልማት /Land Development/

12.4.3.8 በታወቀ ወይም ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ የአፈርና የውሃ ምርመራ መካሄድ አለበት

12.4.4 የግንባታ ፈቃድ

12.4.5 የግንባታ ዋጋ ዝርዝርና ዋጋው የተሠራበት መነሻ ረቂቅ/Take of sheet/ በዶክመንትና በዲስኬት /hard and soft copy/ ወይም

የጨረታ ዶክመንትን በተመለከተ፣

- ጨረታ የወጣበት ዶክመንት / Invitation to bid/
- የጨረታ ግምገማ የተካሄደት መረጃ /Bid analysis/
- የጨረታው አሸናፊ የተሰጠበት /Award/
- ሁሉም መነሻ ዶክመንቶች /All source documents/

<u>ማስታወሻ፣</u> ከቁጥር 12.4.1 — 12.4.3.4 ፣12.4.4 እና 12.4.5 ለሁሉም ኘሮጀክቶች አስፈላጊ ሲሆኑ

ከቁጥር 12.4.3.5 — 12.4.3.8 ያሉት ግን ለእርሻው ዘርፍ በተጨማሪነት የሚያስፈልጉ መረጃዎች ናቸው፡፡

## 12.5 የዋጋ መግለጫዎች (Performa) ወይም የፀደቀ የጨረታ ውጤት ዶክመንትን ስለማቅረብ

12.5.1 ከትንሽ እስከ መካከለኛ ላሉ የብድር ጥያቄዎች አመልካቾች ቢያንስ ለእያንዳንዱ እቃ ሶስት የዋጋ መግለጫዎችን /Performa Invoices/ ከታወቁ ሶስት የተለያዩ አቅራቢዎች ማምጣት ያለባቸው ሲሆን የዋጋ መግለጫዎቹ የእቃውን መለያ /Major Specification/ ብዛቱን /Quantity/፣ ይዘቱን /Quality/ እና ዋጋውን /Price/ አካቶ የያዘ መሆን አለበት፡፡

ሆኖም የእቃው አቅራቢ አንድ ብቻ ከሆነ አንድ የዋጋ መግለጫን ባንኩ ሊቀበል ይችላል፡፡

በጨረታ ለተመረጠ አቅርቦት /ግዥ/ የጨረታው ሰነድና ውጤት መቅረብ አለበት፡፡

በሁሉም አይነት የሚቀርቡት የዋጋ ማቅረቢያዎች ከብድር ጥያቄው ማመልከቻ ጋር ተሟልተው በሚከተሉት ዝርዝሮች መሠረት መቅረብ አለባቸው፡፡

12.5.1.1 መሣሪያዎችና እቃዎች /Machineries and Equipment/ /ብራንድ፣ ሞዴል፣ የተመረቱበት ዓመት፣ የማምረት አቅም /ካፓሲቲ/፣ የተሠሩበት ሀገር፣ መለዋወጫና ተጓዳኝ መሣሪያዎች ያሉት መሆኑን የሚያሳይ/

12.5.1.2 የጥሬ እቃ አቅርቦትና ማሸጊያ

12.5.1.3 ተሽከርካሪ

12.5.1.4 ለኘሮጀክቱ የሚገዙ የቢሮ ዕቃዎች፤ ሌሎች ቋሚ ንብረቶችንና አላቂ ዕቃዎችን የያዙ የዋጋ መግለጫዎች

12.5.1.5 ግሪን ሀውስ (Green House)

12.5.1.6 የአበባ ችግኞች

12.5.1..7 የኬሚካልና ማዳበሪያ ግብአቶች ዋጋ መግለጫ

12.5.1.8 የመስኖ ሥራ

12.5.1.9 የእርሻ መሣሪያዎችና ሌሎችም

12.5.2 የታደሱ /Refurbished/ መሣሪያዎችን በዋስትናነት የሚያቀርቡ የትልልቅ ኘሮጀክቶች ብድር ጠያቂዎች የዋጋ መግለጫ /Performa invoices/ እንዲያቀርቡ አይገደዱም፡፡ መሠሎቹን መሣሪያዎች በተመለከተ ባንኩ የራሱን ፍተሻና ጥናት ያደርጋል፡፡

## 12.6. የዕቃ ግዥ ሂደት

ለኘሮጀክቱ የእቃና አገልግሎት ፍላጐት ማሟያ በባንኩ ብድር የሚካሄዱ ግዥዎች በብሔራዊ ህግ መሠረት የሚተገበሩ ናቸው፡፡

## 12.7. አቅርቦት (Utilities)

በሚቋቋመው ኘሮጀክት አካባቢ የውሃ አቅርቦት፣ የስልክ፣ የመብራት፣ የኢንተርኔትና የፋክስ አገልግሎት መኖሩን የሚያረጋግጥ መረጃ ከሚመለከታቸው ባለሥልጣናት ማቅረብ

## 12.8. ለንግድ ማህበራት/ድርጅቶች የሚሰጥ ብድር

ለአዲስና ለማስፋፊያ ብድሮች ጥያቄ መሟላት ከሚገባቸው መረጃዎች በተጨማሪ ማህበራት/የንግድ ድርጅቶች የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ አለባቸው፡፡

12.8.1 የመመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ ቅጅ

12.8.2 የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ለማህበራት/

12.8.3 በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ያልተገለፁ ከሆነ የሥራ አስኪያጁን/ጇን ከባንክ የማህበሩን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት አስይዞ/ይዛ የመበደር ልዩ የውክልና ሥልጣን

12.8.4 የካፒታል መጨመር ካለ ስለመጨመሩ በጉባኤ የፀደቀና የተመዘገበ ውሣኔ

## 12.9. ውክልና

በውክልና /በሶስተኛ ወገን/ ለሚቀርብ የብድር ጥያቄ በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ ያስፈልጋል፡፡

## 12.10 የጋብቻ ሁኔታን የሚገልጽ ማስረጃ/ በግል ድርጅት ለሚያቋቁሙ

### 12.10.1 የኢትዮጵያ ዜግነት ላላቸው

- ላገቡ፤ የጋብቻ የምስክር ወረቀት
- ላላገቡ፤ ከሚመለከተው ከተማ/ክፍለ ከተማ ፎቶግራፍ ያለበት ያላገቡ መሆኑን የሚገልጽ የምስክር ወረቀት
- ጋብቻቸውን ያፈረሱ፤ ጋብቻው የፈረሰ መሆኑን የሚገልጽ ሰርተፊኬትና ያላገቡ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ

### 12.10.2 ለውጭ ዜጐች

- ላገቡ፤ በሀገራቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የጋብቻ ምስክር ወረቀት
- ላላገቡ፤ ያላገቡ መሆኑን የሚልጽና በሀገራቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፀደቀ መረጃ

## 12.11. የብድር መረጃ

የብድር መረጃ /ስለተበዳሪው/ እና ሌሎችም የተበዳሪውን ታሪክ (Background) የሚዳስስ ጥናት መካሄድ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪ ባንኩ የብድር ደረጃና ሌሎችንም አስፈላጊ ምርመራዎችን እንዲያካሂድ አመልካቾች ቀደም ብሎ ከሌሎች ባንኮች ጋር ስላላቸው ግንኙነት አስፈላጊ የሆኑትን ማስረጃዎች ማቅረብና መፍቀድም ይኖርባቸዋል፡፡

## 12.12. ቅድመ - ኘሮጀክት ጥናት (Feasibility Study)

12.12.1 የኘሮጀክቱን ሁለንተናዊ ገጽታ የሚያሳይ ዝርዝር የኘሮጀክት ጥናት፣ (Feasibility Study) ጥናቱም በመልካም ስማቸው በታወቁና ፈቃድ ባላቸው አማካሪ ድርጅቶች የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል፡፡

12.12.2 የአማካሪው የዘመኑ የታደሰ የሥራ ፈቃድ ቅጂ

12.12.3 የቅድመ ፕሮጀክት ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ሁኔታዎች መያዝ ይኖርበታል፡፡

12.12.3.1 የፕሮጀክቱ ማጠቃለያ

12.12.3.2 የፕሮጀክቱ አመሠራረት /ታሪካዊ አመጣጥ/

12.12.3.3 የገበያ ጥናት

1212.3.4 ቴክኒካዊ ጥናት

12.12.3.5 የመዋቅር፣ ማኔጅመንትና የሰው ኃይል ጥናት

12.12.3.6 ፕሮጀክቱ የሚተገበርበት የጊዜ ሰሌዳ

12.12.3.7 የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥናት

12.12.3.8 የፋይናንስ ጥናት

12.12.3.9 ማጠቃለያና አስተያየት /Conclusion & Recommendation/

12.12.3.10 ደጋፊ ሰነዶችና ሌሎች ተያያዥ ማስረጃዎች

## 12.13. ነባር ድርጅቶችን ከሚያስፋፉ አመልካቾች የሚፈለጉ መረጃዎች

12.13.1 ከቁጥር 12.1 እስከ 12.12 የተመለከቱት መረጃዎች ሁሉ

12.13.2 የንግድ ሥራ ፈቃድ

12.13.3 የነባሩ ድርጅት ቋሚና አላቂ ንብረቶች ዝርዝር እና የዋጋ ግምት የተገዙበትን ዘመንና ዋጋ የሚገልጽ ሠነድ

12.13.4 የተመዘገበው ካፒታል በቂ ካልሆነ፤ የማስፋፊያ ፈቃዱ ከተጨማሪው ካፒታል ጋር

12.13.5 ቢያንስ የመጨረሻዎቹ ሶስት ዓመታት በታወቀ የሂሣብ መርማሪ /ኦዲት/ ድርጅት የተመረመረ የድርጅቱ የሂሣብ መግለጫ

12.13.6 ለተጨማሪ መሬት ማልሚያ ሥራ /ግንባታ ሥራ/ የሚውል ዝርዝር ዋጋና ፕላን

12.13.7 የፕሮጀክቱ የቀድሞ የሥራ ውጤት

12.13.7.1 ምርት

12.13.7.2 አጠቃላይ ለውጭ ገበያ የቀረበው ምርት ብዛትና ዋጋ

12.13.7.3 የሀገር ውስጥ ሽያጭ ብዛትና ዋጋ

12.13.7.4 ከሀገር ውስጥ ሽያጭ የተገኘው ገቢ

12.13.7.5 ፕሮጀክቱ ያረፈበት ጠቅላላ ስፋት

**12.13.7.6** ለተለያዩ ምርቶች የተመደበው የቦታ ስፋት

**12.13.7.7** ከእያንዳንዱ የምርት ዓይነት የተገኘው ምርት መጠን

**ማስታወሻ፣** ከቁጥር 12.13.7.1 — 12.13.7.4 ያሉት ለሁሉም ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ ሲሆን ከቁጥር 12.13.7.5 — 12.13.7.7 ለእርሻ ፕሮጀክቶች ብቻ የሚቀርቡ ናቸው።

## 12.14. ለአንድ ተበዳሪ የሚሰጥ የብድር ወሰን

12.14.1 የአንድ ደንበኛ ግለሰብ ወይም የንግድ ድርጅት የሚኖርበት ጠቅላላ እዳ ከባንኩ ካፒታል 25 % መብለጥ የለበትም።

12.14.2 በአንድ ድርጅት ጥላ ሥር የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች ከባንኩ በተሰጣቸው አንድና ከዚያ በላይ ብድር የሚኖርባቸው ጠቅላላ እዳ ከባንኩ ካፒታል 35% ድርሻ መብለጥ የለበትም።

## 12.15. የብድር መክፈያ ጊዜ

ብድሩ ተመላሽ የሚሆንበት ጊዜ የሚወሰነው በፕሮጀክቱ የገንዘብ ማመንጨት አቅምና የኢንቨስትመንት እቃዎች ኢኮኖሚያዊ ግልጋሎት እድሜ ታይቶ ነው።

## 12.16. ዋስትና

ባንኩ በይበልጥ የሚተማመነው በፕሮጀክቱ አዋጭነትና ትርፋማነት ላይ ነው። ሆኖም ብድሩን ለመጠበቅ ሲባል ባንኩ ለሁሉም ብድሮች አንደኛ ደረጃ ዋስትና ይይዛል። በባንኩ የብድር ፖሊሲ መሠረት የዋስትና ንብረቶችን ባንኩ በየአመቱ ይገምታል።

## 12.17. ወለድ

በብድር ላይ ባንኩ የሚያስከፍለው ወለድ መጠን በባንኩ አመራር ቀርቦ የባንኩ ቦርድ ከመንግሥት ጋር በመመካከር ካፀደቀው በኋላ ሥራ ላይ የሚውል ነው።

በአሁኑ ጊዜ ባንኩ የሚያስከፍለው ወለድ ቅድሚያ ለተሰጣቸው ፕሮጀክቶች በዓመት 7.5 % /ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ/ ነው።

## 12.18. የግዴታ ክፍያ /Commitment charge/

ብድሩ ተፈቅዶ የብድር ውል ከተፈረመ በኋላ ወጪ ሆኖ ባልተወሰደ ብድር ላይ ደንበኛው በየዓመቱ 0.5 % /ነጥብ አምስት በመቶ/ የግዴታ ክፍያ ይጠየቃል፡፡

## 12.19. የሂሣብ መዛግብት ማዘጋጀት

12.19.1 የባንኩ ተበዳሪ ትክክለኛና ተቀባይነት ያለው የሂሣብ መዛግብት ሊኖረው ይገባል፡፡ ተበዳሪው በታወቀ የሂሣብ ባለሙያ የተመረመረ የሂሣብ መዛግብት ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

12.19.2 ባንኩ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች የያዘ የተበዳሪውን ድርጅት አመታዊ የሥራ እቅድ /ፕላን/ ይጠይቃል፡፡

- ድርጅቱ ያለው ጥንካሬ፣ ድክመት፣ አመቺ እድልና ስጋት /SWOT/
- ለውጭ ገበያ እንዲቀርቡ በእቅድ የተያዙ ሥራዎችንና የገበያ ሁኔታ
- የሽያጭና የወጭ ሁኔታ ትንበያ፣ ለዚህም የሚረዱትን ታሳቢዎች በማስደገፍ፤
- የእዳ ክፍያ መረጃ፤
- ድርጅቱ በሚቀጥለው ዓመት ሊተገብረው ስላቀደው ሥራ አስፈላጊውን መረጃ፤

12.19.3 የተፈቀደውን ብድር እንዴት በሥራ ላይ እንደዋለ የሚያሳይ ትክክለኛና ተቀባይነት ያለው የሂሣብ መዛግብት ተበዳሪው እንዲይዝ ያስፈልጋል፡፡

12.19.4 ባንኩ በሚያስፈልግበት ወቅት የተበዳሪውን የሂሣብ መዛግብት የማየት መብት ይኖረዋል፡፡

## 12.20. የመሐንዲስ ግምት

ባንኩ ብድር ከመልቀቁ በፊት በሥራ ላይ የዋለውን ግንባታ በመገመት የብድሩ ቅድመ ሁኔታ መሟላቱን ያረጋግጣል፤

## 12.21. መድህን

የኘሮጀክቱ ቋሚ ንብረቶችም ሆኑ በዋስትና የሚያዙ ንብረቶች ብድሩ ሙሉ በሙሉ ተመላሽ ሆኖ እስከተከፈለበት ጊዜ ድረስ ባንኩ የጋራ ተጠቃሚ የሚሆንበት የመድን ዋስትና እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡

## 12.22. ብድሩ እንዲለቀቅ የሚቀርብ ማመልከቻ /Application Letter/

ደንበኛው የሚለቀቀውን ብድር ለምን ዓላማ እንደሚያውለው በመጥቀስ ብድሩ እንዲለቀቅለት በጽሑፍ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

## 12.23. የሚንቀሳቀስ ሂሣብ

ደንበኛው የተፈቀደው ብድር ከመለቀቁ በፊት በባንኩ የሚንቀሳቀስ ሂሣብ መክፈት ይኖርበታል፡፡

## 12.24. የመተማመኛ ሰነድ (Letter of Credit /L/C)

ተበዳሪዎች ከውጭ ለሚያስገቧቸው እቃዎችና ወደ ውጭ ለሚልኳቸው ምርቶች በባንኩ የመተማመኛ ሰነድ መክፈት ይኖርባቸዋል፡፡

## 12.25. የዕቃ ግዥ ሂደት

ሀገሪቱ ከምትቀበለው ዓለም አቀፍ ስምምነት በማይቃረን መልኩ፣ ባንኩ ብድር ለሚሰጣቸው ኘሮጀክቶች የሚያስፈልጉት እቃዎችና አገልግሎት መቅረብ ያለበት በገበያ ውድድር ተመስርቶ መሆን ይገባዋል፡፡

## 12.26. ሌሎች ሁኔታዎች

- ተበዳሪዎች በኘሮጀክት ጥናት ውስጥ እንደተጠቀሰው የሥራ ልምድ ያላቸውን በሙያቸው የተካኑ ሠራተኞችን ቀጥረው ማሠራት ይኖርባቸዋል
- ባለቤቱ ኘሮጀክቱን በተጨማሪ እንደ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚሠራ ከሆነ፣ በኘሮጀክቱ ጥናት ውስጥ እንደተጠቀሰው የሥራ አመራር ችሎታ ለሥራው በሚመጥን መልኩ ማሟላት ይኖርበታል/ይኖርባታል፡፡

## 13. <u>ማሳሰቢያ ለብድር ጠያቂዎች</u>

- ባንኩ በየጊዜው እያደገ የሚሄደውን የደንበኞች ፍላጎት ለማርካት የሚያስችለውን የመሠረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ ጥናት ውጤቶችን ተግባራዊ ማድረጉን ያበስራል፡፡

- ማንኛውም ኩባንያ፣ ማኅበር ወይም ግለሰብ አዲስ ኘሮጀክት ለማቋቋም፣ ወይም የነበረውን ለማስፋፋት ቢፈልግ ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት ወይም ወደ ቅርንጫፍ ቢሮዎች በመሄድ ማማከር ይችላል፡፡
- የባንኩን አገልግሎት ለሚሹና የሚፈለጉባቸውን መረጃዎች ላሟሉ ደንበኞች ባንኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፡፡ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ደንበኞች በሚሰጡት አስተያየት በመታገዝ አሠራሩን ለማሻሻል ምንጊዜም ዝግጁ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ለመግለጽ ይወዳል፡፡
- ስለባንኩ የብድር ፖሊሲ እና ኘሮሲጀር በበለጠ ማወቅ የሚፈልግ ማንኛውም ተገልጋይ ከባንኩ ዋና መ/ቤትም ሆነ ከቅርንጫፍ ቢሮዎች መረጃ ማግኘት ይችላል፡፡
- ቅሬታ ያለው ሰው የባንኩን የዕዝ ሰንሰለት ጠብቆ ማቅረብ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ለባንኩ የሥነ ምግባርና የአገለግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ቢሮ ቅሬታውን በቀጥታ ማቅረብ እንደሚቻል ይገልፃል፡፡

**የኢትዮጵያ ልማት ባንክ**

አድራሻ፡

ዮሴፍ ብሮንዝ ቲቶ መንገድ

የመ.ሣ.ቁ. 1900

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

ስልክ፡ +251-11-551 11 88/89

ፋክስ፡ +251-11-55116 06

Email: dbe@ethionet.et

Website: www.dbe.com.et